# ለቅሶ አልሻም እኔ (ለሳሙኤል አእለማየሁ ከአያልነሽ)

የምን እየዬ ነው የምን እምባ ማፍሰስ
የምን እየዬ ነው የምን ለቅሶ ማልቀስ
እውነትን አንግቦ ፅናትን ለሚያወርስ

የምን እየዬ ነው የምን ሙሾ ማውረድ
በዓላማው ቆሞ በቃሉ ለሚሄድ
እኔስ አላለቅስም ጓዶች አታልቅሱ
ስጦታ ሰቶናል ታሪኩን ውረሱ
ለጥንካሬያችሁ ፅናቱን ልበሱ

የምን እየዬ ነው የምን እምባ ማፍሰስ
ባመነበት ፀንቶ ኩራትን ለሚያለብስ
እውነት ተሸክሞ እውነትን ለሚያወርስ

እኔስ አላለቅስም ለምን አለቅሳለሁ
ገድሉን ዓላማውን በልቤ ይዣለሁ
እስከመጨረሻው ህልሙና ራዕዩን
ፀንቼ አደርሳለሁ

አላለቅስም እኔ አላፈስም እንባ
አጎናፅፎኝ ሄዷል የፅናት ዘንባባ
እንዲያውም በረታሁ ሰጠኝ ጥንካሬ
ቃሉን እንድፈፅም አሸከመኝ ወኔ

ሳሚ!
አውቃለሁ ፅናትህን
የመንፈስ ጥንካሬህን
አውቃለሁ ጀግንነትህን
ለኢትዮጵያ መዋተትህን
ድፍን 34 ዓመት መድከምህን
ለኢትዮጵያ ታላቅነት ሂውትህን መስጠትህን
አሉኝ ሥንክሳሮች
ታሪክህን ዘካሪዎች
ጀግንነትህን መሥካሪዎች
አርበኝነትህን ተራኪዎች
አሉኝ እምቅ ኩነቶች
የፈጸምካቸው ጀብዱዎች
የሰላሳ አራት ዓመት ፀጋዎች
የተጋድሎህ ማህተሞች

ሳሚ!
በትግል መሞት ሂወት
በአመፃ መሞት ሂወት
ዳግም ትንሣኤ ልደት ብለህ ዘምረህ
በፅናትህ ሚሊዮኖችን አስከትለህ
ዓላማህን በአደባባይ ዘርግተህ
ለጓዶችህ ናኝተህ ከጓዶችህ ጋር ቆመህ
ለዘመናት በጭቆና ማጥ በግፍ ሠንሠለት ታስሬ
መብቴን ላስከብር ጠላትን ልሸር ተነሰቻለሁ ዛሬ

ቢወቀጥ አጥንቴ ቢንቀረቀር ደሜ
ለዓዲስ ሥርዓት ልምላሜ
ፍፁም ነው እምነቴ ለትግሉ ነው ሂወቴ
ልጓዝ በድል ጎዳና በተሰውት ጓዶች ፋና
ብለህ
የቀደሙትን ጓዶችህን ቃል ኪዳናቸውን ተቀብለህ
እስከ ሂወትህ ፍፃሜ ዓላማቸውን ይዘህ ተመምህ።

ሳሚ!
ይመስክሩ ይናገሩ
እኒያ ስፍር ቁጥር የሌላቸው እንቁ ጓዶች የሞቱለት
በከተሞች በገጠሮች ደማቸውን የዘሩለት
በፋሽስቶች ወህኒ ቤቶች፥በሥርቻ በአደባባይ
በየአውራ መንገዱ ላይ
አጥንት የከሰከሱ
ሥጋቸውን ያሥቀረሱ
የተነዱ የተጋዙ መከራን የቀመሱለት
በኢህአፓ ሥር ተሰልፈው ሂወታቸውን የገበሩለት
ይናገሩ ስለ እውነት ስለ በላይ ማንነት
ተከትሏቸዋልና አላማቸውን ይዞ በፅናት

ሳሚ!
በትግሉ ውስጥ ተለብልቦ በትግሉ ውስጥ ተፈልፍሎ
ኢትዮጵያዊነትን ተላብሶ ለኢትዮጵያ ትንሣኤ ከፍሎ
የቀደሙትን ጓዶቹን ተከትሎ
እኒያን የሞቱለትን በቃላቸው የፀኑትን
በሥጋቸው በአጥንታቸው በደማቸው ያቆሙትን
አባት ጓዶች፥ እናት ጓዶች፥
አፍላ ጓዶች፥ ወጣት ጓዶች
አደራጅቶ አሁንም የቀሙለትን
አርማቸውን ቀና አድርገው ድምፃቸውን ያቆዩትን
ወኔያቸውን የወረሱ ትግላቸውን ያፀኑትን
ሃያል ጓዶች አቀላልፎ አቀናጅቶ
ባለፉት የትግል ዓመታት
ባለፉት ቀውጢ ሰዓታት
በግንባር ዘልቆ ተዋግቷል
ፊታውራሪ ሆኖ መርቷል
እንደቀደሙት መሰሎቹ ለኢትዮጵያ ብዙ ደክሟል
እንደ ታግለው አታጋዮቹ ለትግሉ ሂወቱን ከፍሏል
በሞቱም ሂወት ዘርቶ ሚሊዮኖችን አሰልፏል
ይህንን ሀቅ ማን ይክዳል የፈለገውን ሰርቶ ሄዷል
እናም
የተፈጥሮ ህግ ነውና ዓለም የተቀበለው
ሰው ሲደክመው ማረፍ ምንጊዜም ያለ ነው
ይህንን እውነታ ማንም ሰው አይሽረው

አለና ተጓዘ ከማይቀረው ሞት
ሲደክመው ዓረፈ ሀሙሱን ጥዋት
ሳሚ!
እኔም ተራው ደርሶኝ እስክከተልህ
ፈጣሪ ነፍስህን በገነት ያኑራት አፈሩ ይቅለልህ።